# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

# 136ኛ ልዩ መግለጫ

**ብሄር ተኮር ማፈናቀልና እንግልት**

**በአስቸኳይ ይቁም!**

www.ehrco.org

የምዝገባ ቁጥር. 1146

**ነሐሴ 2007 ዓ.ም**

# ሰመጉ

## አዲስ አበባ ዋናው ጽ/ቤት

ሳህለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19 (አ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን)

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜል: info@ehrco.org

ዌብሳይት: www.ehrco.org

## የሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ

ስልክ: (+251) 011 551-4489

ኢሜል: complaints@ehrco.org

## የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

## የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ባህርዳር፡ ስ.ቁ (+251) 058 226-3913 ፖ.ሳ.ቁ 1115

ሐዋሳ፡ ስ.ቁ (+251) 046 220-4500 ፖ.ሳ.ቁ 360

ነቀምት፡ ስ.ቁ (+251) 057 661-5014 ፖ.ሳ.ቁ 463

ጅማ ፡ ስ.ቁ (+251) 147 211 5434

ድሬደዋ፡ ስ.ቁ (+251) 025 811 9150

# ማውጫ

1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ---------------------------------------- 1

2. የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ------------------------------------------------------------ 2

3. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ አሎ ቀበሌ የተፈፀ የመብት ጥሰት 3

   የመብት ጥሰቱ የኋላ ታሪክ ----------------------------------------- 3

4. ቤት ንብረት የተቃጠለባቸው፣ ከመኖሪያ ቤታቸውና ከእርሻ መሬታቸው የተፈናቀሉ


   አርሶ አሰደሮች ስም ዝርዝርና የጉዳቱ መጠን ------------------------------------------ 4

5. የመብት ጥሰቱ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ ------------------------------------------------ 7

6. ማጠቃለያ -------------------------------------------------------------------------------------- 7

7. ማሳሰቢያ ----------------------------------------------------------------------------- 8

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




| |
|---|
| የመብት ጥሰቱ የደረሰበት ቦታ |

[1] "ኢትዮጵያ" [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (May 18, 2011)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግስታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሰመጉ ከተቋቋመበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 23 አመታት ሁለንተናዊ ሀገራዊ ተልዕኮ በመያዝ በቆመላቸው አበይት አላማዎች ላይ በመመርኮዝ በነደፋቸው በርካታ ፕሮግራሞች አማካኝነት የሰብአዊ መብት መከበርን፣ የህግ የበላይነትን እና ህጋዊ ስርአትን በማራመድ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋፆ አበርክቷል እያበረከተም ይገኛል፡፡

ይህን ተልእኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትህ እንዲያገኙ፣ የጥሰቱ ፈፃሚዎች በህግ እንዲጠየቁ፣ የሰብአዊ መብት ግንዛቤ በህዝብና በመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ዘንድ እንዲዳብር፣ የተፈፀሙ ጥፋቶች እርማት እንዲያገኙ በአጠቃላይም የህዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ብዙ ሰርቷል፡፡

ዋና ዋናዎቹ የሰመጉ የመርሐግብር ተግባራትም፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መከታተልና ለሚመለከታቸው የመንግስት የስራ ሀላፊዎች በማሳወቅ እንዲታረም ማድረግ፣ የህግ ድጋፍ መስጠት፣ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ በሰብአዊ መብቶች ላይ ትምህርት መስጠት፣ የወጡና የሚወጡ ህጎች በትክክል ስለመተግበራቸው መከታተል፣ የሰብአዊ መብት አያያዝን መከታተል፣ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብአዊ መብቶቻቸው መጠበቁን ማረጋገጥና እንዲሁም መመርመር እና መግለጫ ማውጣት ናቸው፡፡

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36ኛ መደበኛ መግለጫዎችና 135ኛ ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል፡፡ ከእነዚህም ባሻገር ህዝቡ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ትግበራ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል ተከታታይ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት የአድቮኬሲ እና የህግ ድጋፍ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም አቅም በፈቀደለት መጠን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የፀና አላማ አኳያ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 11(1) እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መጠለያን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ ኑሮ የማግኘት መብት እንዳለውና መንግስት ደግሞ የዚህ መብት የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ይህ ቃል ኪዳን ይደነግጋል፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 32/1/ «ማንኛውም ኢትዮጵያ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት ነፃነት አለው" ሲል በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ይሁንና ከዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከዚህ በታች የተዘረዘረው የመብት ጥሰት በዜጎች ላይ ተፈፅሟል፡፡

## 3. በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ አሎ ቀበሌ የተፈፀመ የመብት ጥሰት

### የመብት ጥሰቱ የኋላ ታሪክ

በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች የተለያዩ አይነት ሰብሎችን በመዝራት ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን ክልሉንና በአጠቃላይም ለሀገሪቱ ገበያ የሚቀርብ ምርት በማምረት የሚታወቁ ውጤታማ አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ ይሁንና በአካባቢው የሚገኙ ባለስልጣናትና የጸጥታ ሀላፊዎች እነዚህን አርሶ አደሮች "እናንተ የዚህ አካባቢ ተወላጅ ሳትሆኑ ሀብት እያፈራችሁ የአካባቢው ተወላጆች ግን ከናንተ ያነሰ ገቢ ነው ያላቸው… ይህን ገቢ ያገኛችሁት በኛ መሬት ነው፣ ስለዚህ የክልሉ ተወላጆች ባለመሆናችሁ ክልሉን ለቃችሁ ውጡ" በማለት ንብረታቸውን በተለያየ ጊዜ በመንጠቅ እነዚህንም አርሶ አደሮች በተለያዩ ጊዜያት ለህገወጥ እስራት ዳርገዋቸዋል፡፡ የአካባቢውን ተወላጅ ህዝብም "በናንተ መሬት ነው ሀብት ያፈሩት …" እያሉ ጥላቻንና ግጭትን ሲሰእኩ ቆይተዋል፡፡[2]

በተለይም መጋቢት 27 2007 ዓ.ም አቶ ዘመዱ እንዳለ የተባለ የኦሮሞ ብሔረሰብ ተወላጅ ተገድሎ ይገኛል፡፡ እዚህ ላይ ለጊዜው ስሙን የማንገልጸው የግድያ ድርጊቱ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ሥር ውሎ ጉዳዩ ውሳኔ ሣያገኝ፣ ይህ "ግድያ የተፈፀመው በአማራ ብሔረሰብ ተወላጆች ነው" በማለት የኖኖ ወረዳ የፖሊስ አዛዥ የሆኑት ኢንስፔክተር ሀይሉ ድሪባ፣ የናኖ አሎ ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ ጎሳዬ ገች እና መቶ አለቃ ገነነ በየነ የተባሉ የፖሊስ አባላት የቀበሌ አመራሮችንና የፖሊስ አባላትን በማስተባበር የአካባቢው ህዝብ በአካባቢው በሚኖሩ የአማራ ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ እንዲነሳ በማነሳሳት ሚያዝያ 9 2007 ዓ.ም 85 አርሶ አደር አባወራዎችን ለእስራት ከዳረጉዋቸው በኋላ ቅዳሜ ማለትም ሚያዝያ 10 2007 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰዓት አካባቢ ዘር በመምረጥ የአማራ ብሔረሰብ ተወላጆች መኖሪያ ቤትና ንብረት ነው ያሉትን እየመረጡ በእሳት እንዳቃጠሉ የታሰሩትንም አባወራዎች ከእያንዳንዳቸው 300 ብር ለነዳጅ ብለው ከተቀበሉዋቸው በኋላ ቤታችሁ ተቃጥሏል፣ ሂዱ በማለት ከእስር እንደለቀቀዋቸው ለሰመጉ በቀረበ ማመልከቻና የሰመጉ ባለሙያዎችም በአካባቢው ለማጣራት በሄዱበት ወቅት ያነጋገሩዋቸው ቤት ንብረት የተቃጠለባቸው አርሶ አደሮች አስረድተዋል፡፡[3] የሰመጉ ባለሙያዎች ከኖኖ ወረዳ አስተዳዳሪ ጋር ሁት ጊዜ በስልክ ግንኙነት አድርገዋል፡፡ የወረዳው አስተዳዳሪ በዚህ መግለጫ ውስጥ የተጠቀሱት ቤቶች ከነሙሉ ንብረታቸውን ቤቶቹ በተቃጠሉበት ቦታ ላይ 24 የቆርቆሮ ሥራ መጀመሩን፣ ቤት ለተቃጠለባቸው እና ንብረት ለወደመባቸው ዜጎች የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት በራስ ተነሳሽነት ገንዘብና እህል አዋጥተው ለተጎጂዎች እርዳታ እንዲደርሳቸው እየተደረገ መሆኑንና ተጎጂዎቹ ተረጋግተው እንዲኖሩ ለማድረግ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሠራ መሆኑን አተዳዳሪው ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአካባቢው ሕዝብ በራሱ ተነሳሽነት የዕርዳታ ገንዘብና እህል ማዋጣቱ ቢረጋገጥም እርዳታው ግን ይህ መግለጫ እስከተዘጋጀበት ደረስ ለተጎጂዎቹ አለመድረሱን ሰመጉ አረጋግጧል፡፡

### የደረሰ የንብረትና የህይወት ጉዳት በቁጥር

- የ1 ሰው ህይወት አልፏል
- 10 ሰዎች ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል
- 99 የሳር ክዳን ቤቶች በእሳት ተቃጥለው ወድመዋል
- 25 የቆርቆሮ ክዳን መኖሪያ ቤቶች በእሳት ተቃጥለው ወድመዋል

---

[2] የሰመጉ ባለሙያዎች በአካባቢው ለማጣራት በሄዱበት ወቅት ከተጎጂዎች የምስክርነት ቃል የተወሰደ

[3] ለሰመጉ በጽሁፍ የቀረበ ማመልከቻ ቀን 28/08/2007 ዓ.ም አዲስ አበባ

የአርሶ አደሮቹን መኖሪያቤትና ንብረት ቃጠሎ ተከትሎ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች፣ ህፃናትና አቅመደካሞች የሚገኙባቸው ተፈናቃዮች ከአካባቢያቸው በመሰደድ ወደ ደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን ሀበሽጌ ወረዳ ድንኳን ውስጥ ተጠልለው ሲረዱ ቆይተዋል፡፡



[4] ፎቶ ግራፍ 1፡ ሟች አቶ ዳመና ግዛው ሚያዝያ 10 2007 ዓ.ም በፖ`ሊስ ኩላሊታቸው ላይ ተረግጠው ህይወታቸው ያለፈ የቀብር ስነስርአታቸውም በ11/08/2007 ዓ.ም በዳርጌ ማርያም ተፈፅሟል፡፡

## 4. ቤት ንብረት የተቃጠለባቸው፣ ከመኖሪያ ቤታቸውና ከእርሻ መሬታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች ስም ዝርዝርና የጉዳቱ መጠን

ሰንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የአርሶ አደሩ ስም | የሚኖርበት አድራሻ | | | | የተቃጠለ ቤት | | የተቃጠለበት የእህል አይነት | | | | | የተቃጠሉ የቤት እቃዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ | የቆርቆሮ | የሳር | ጤፍ | በቆሎ | ማሽላ | ሽምብራ በሎቄ | በርበሬ | አልጋ | ሳጥን | ብር | ጠቅላላ ግምት |
| 1 | ፀጋዬ ብርዙ | ኦሮሚያ | ም/ሸዋ | ናኖ | ናኖ አሎ | | 4 | 8 | 15 | 20 | 15 | 300 | 2 | 2 | 53,000.00 | 250,000.00 |
| 2 | ዝናው ዘለቀ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | 8 | 110 ኩ | 14 ኩ | 7 | 100ኪ. | 2 | 2 | 68,000.00 | 250,000.00 |
| 3 | ወ/አገኝ ብርዙ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 3 | 5 | 10 | 2 | 200ኪ. | 2 | 1 | 22,000.00 | 63,000.00 |
| 4 | ተሾመ እርገጤ | ›› | ›› | ›› | ›› | 2 | 2 | 8 ኩ | 150 | 20 | 2 | 300ኪ. | 1 | 1 | 25,000.00 | 312,000.00 |
| 5 | ደጉ አባይነህ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 12 | 155 | 30 | 8 | 500ኪ. | 2 | 1 | 30,000.00 | 600,000.00 |
| 6 | ጌትዬ አባይነህ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | | | | | | | | |
| 7 | አውራሪስ ደርቤ | ›› | ›› | ›› | ›› | 2 | 4 | 8 | 20 | 85 | 15 | 500 | 2 | 1 | 468,000.0 | 900,000.00 |
| 8 | ሞገስ የሻነው | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 3 | 30 | 12 | 10 | 1500ኪ. | 1 | 1 | 61,500.00 | 275,000.00 |
| 9 | ቦጋለ ተያዘ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 4 | 6 | 40 | 15 | | 200 | 1 | 1 | 120,000.0 | 200,000.00 |
| 10 | አስቻለው በሀሩ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 20ኩ | 200 | 30 | 10 | 4ሺ. | 2 | 2 | 250,000.0 | 1,500,000.00 |
| 11 | ማሞ ሞገስ አየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 4 | 1 | 10 ኩ | 3 | | 200 | 3 | 1 | 11,000.00 | 150,000.00 |
| 12 | በፍቃዱ አንፈራጥ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 4 | 32 | 11 | 5 | 200 | 2 | 1 | 11,330.00 | 90,000.00 |
| 13 | ሹመዬ ሀብታሙ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 3 | 50ኪ. | 1 ኩ | 13 | 3 | 200 | 1 | | 2,500.00 | 50,000.00 |
| 14 | በፍቃዱ እጅጌ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | 30 ኩ | 15 | 1 | 150 ኪ. | 1 | | 29,000.00 | 69,000.00 |
| 15 | ዓለሙ መኮንን | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 2 | 45 | 3 | 300 | 1 | | | 80,000.00 |
| 16 | ስመኝ እንግዳ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 1 | 7 | 6 | 1 | 100ኪ. | 1 | | 15,000.00 | 30,000.00 |
| 17 | በድሉ በፈቃዱ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | | | | | | | |
| 18 | አበራ ሲመቸው | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | 5 | | 400ኪ. | 1 | | 3,000.00 | 68,000.00 |
| 19 | አለበስ ታየ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | 10 | 5 | 1 | 300 | 1 | | 16,000.00 | 60,000.00 |
| 20 | ሲሳይ ሀብታሙ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 30 | 5 | | 50ኪ. | 1 | | 20,000.00 | 50,000.00 |
| 21 | አዲሱ ታምር | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 3 | 40ኩ | 9 | 2 | 300 | 1 | | 18,700.00 | 75,000.00 |
| 22 | ኩራዝ ታዬ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | | 16ኩ | 2 | 1 | 150 | 1 | | 11,000.00 | 41,000.00 |
| 23 | ታዬ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 1 | 20 | 1 | 1 | | 1 | | 15,000.00 | 46,000.00 |
| 24 | አውራሪስ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 5 | 100 | 20 | 15 | 100 | 4 | 1 | 50,000.00 | 4,000.00 |

| ተ.ቁ | የአርሶ አደሩ ስም | የሚኖርበት አድራሻ | | | | የተቃጠለ ቤት | | የተቃጠለበት የእህል አይነት | | | | | የተቃጠሉ የቤት እቃዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ | የቆርቆሮ | የሳር | ጤፍ | በቆሎ | ማሽላ | ሽምብራ ቦሎቄ | በርበሬ | አልጋ | ሳጥን | ብር | ጠቅላላ ግምት |
| 25 | ዘመድኩን ዳኜ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | | 1 | 1 | 3 | | 2 | | 80,000.00 |
| 26 | ሸዋንዳኝ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 3 | | 50ኩ | 30 | | | | | 20,000.00 | 80,000.00 |
| 27 | ቄስ ሽፈራ ጠጁ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 3 | 15ኩ | 10 | 1 | 200 | | 1 | | 181,000.00 |
| 28 | ብርቁ ደለለኝ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 50ኩ | 7 | | 50 | 1 | | 7,000.00 | 40,00.00 |
| 29 | ጉቺል ደለለኝ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | 4 | 32 | 24 | 4 | 300 | 2 | 1 | 32,000.00 | 110,000.00 |
| 30 | ደምስ ደለለኝ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 4 | 22 | 4 | | 100 | 1 | | 6,000.00 | 35,000.00 |
| 31 | ደሞዝ አበበ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 4 | 30 | 4 | 1 | 100 | 1 | 1 | 6,000.00 | 120,000.00 |
| 32 | ሀብታሙ ክብረት | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | 15 | 32 | 25 | 4 | 200 | 1 | 3 | 75,000.00 | 586,000.00 |
| 33 | ዳጄ ጠናጋሻው | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | | 1 ኩ | | 3 | 2 | 50 | 1 | 1 | 46,500.00 | 78,000.00 |
| 34 | ዘገየ ነጋ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | 7 ኩ | 40ኩ | 3 | | 300 | 1 | 1 | 15,000.00 | 80,000.00 |
| 35 | ስጦታው እሸቱ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 2 | | 8 | 2 | 300 | | | 18,000.00 | 50,000.00 |
| 36 | አናውጠው ተስፋዬ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | | 60ኩ | | | 200 | 1 | | | 50,000.00 |
| 37 | ሸዋቀና ታደሰ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | | | 3 | | 150 | 2 | 1 | 6,000.00 | 35,000.00 |
| 38 | ትብልጥ አበባው | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | 5 ኩ | 75ኩ | 13 | 7 | 300 | 2 | 1 | 108,000.0 | 280,000.00 |
| 39 | አበራ አሂደው | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 10 | 8 | 2 | 300 | 2 | | 5,000.00 | 63,000.00 |
| 40 | አይለ ግርማ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | | 65 | 9 | 1 | 300 | 1 | | 36,000.00 | 300,000.00 |
| 41 | አረጋኸኝ ታደ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 20 | 10 | 2 | 300 | 1 | | | 90,000.00 |
| 42 | ባፈቀድ አድማሱ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 1 | 32 | 7 | 1 | 300 | 1 | | 5,000.00 | 75,000.00 |
| 43 | አወራሪስ አድማሱ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 5 | 35 | 10 | 10 | 100 | 2 | 2 | 10,000.00 | 95,000.00 |
| 44 | ገለታው ስጠግን | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 4 | 35 | 12 | 4 | 300 | 2 | 1 | 18,000.00 | 85,000.00 |
| 45 | አይኩሩ ጥበቡ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | 30 | 24 | | | 2 | 1 | 70,000.00 | 113,000.00 |
| 46 | አስፋው ወርቁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | | | | | | | | | 30,000.00 |
| 47 | ምንዳ ግርማዬ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | 1 | 25 | 7 | | 60 | | | 7,000.00 | 50,000.00 |
| 48 | ሸዋንዳኝ ንጉሴ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | | 30 | 15 | 1 | 200 | 1 | | 5,000.00 | 81,000.00 |
| 49 | ማሞ አሰፋ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 2 | 4 | 100 | 25 | 15 | 1000 | 2 | 1 | 40,000.00 | 325,000.00 |
| 50 | አጥላው አበባው | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 50 | 8 | 3 | 200 | 2 | 1 | 30,000.00 | 97,000.00 |
| 51 | ጣሰው ተፈራ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | | | | | | | |
| 52 | አበበ ማሞ | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | | | 22 | | 8 | | | | | 150,000.00 |
| 53 | መሰለ አልዩ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | 8 | 2 | | | 1 | | 3,000.00 | 20,000.00 |
| 54 | ታምር ጠጋው | ›› | ›› | ›› | ›› | 1 | 1 | | 47 | 11 | | 150 | 1 | | | 100,000.00 |
| 55 | ስለወንድም አንፈራጥ | ›› | ›› | ›› | ›› | 2 | 2 | 8 | 180 | 30 ኩ | 4 | 200 | 1 | 1 | 10,000.00 | 300,000.00 |
| 56 | የምሩ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 1 ኩ | 27 | 6 | 1 | 50 | 1 | | | 40,000.00 |
| 57 | ሲያምረኝ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | | | 6 | 1 | 150 | 1 | | | 20,000.00 |
| 58 | እትማልሽ ንጉሴ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 2 | | | | 50 | 1 | | | 17,000.00 |
| 59 | ጌቶ ገበየሁ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | | | | | 50 | | | 8,000.00 | 35,000.00 |
| 60 | ፋሲካው ልብሴ | ›› | ›› | ›› | ›› | | 2 | 2 | 5 | 6 | 2 | 150 | 1 | 1 | 5,000.00 | 15,000.00 |
| 61 | መኮንን ወርቁ | ›› | ›› | ›› | ›› | 3 | 2 | 50ኩ | 500 | 60ኩ | 40 | 6000 | 3 | 1 | 200,000.00 | 1,900,000.00 |
| 62 | ደጀኔ መኮንን | ›› | ›› | ›› | ›› | | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1000 | | | | 94,000.00 |
| 63 | ታዬ ባዩ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | | | 800 | | | 40,000.00 | 125,000.00 |
| 64 | አይደፈር እርገጤ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | | | | | | 5,000.00 | 20,000.00 |
| 65 | ካሳው መልሰው | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | 2 | 20 | 10 | | 20 | 1 | 5,000.00 | 60,000.00 |
| 66 | ጌታቸው አምታው | ›› | ›› | ›› | ›› | | | 2 | | | 1 | | | 1 | 10,000.00 | 14,000.00 |
| 67 | አሰጥሌ ጠጋው | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | | | | | | 12,000.00 | 12,000.00 |
| 68 | ክበብ ግርማዬ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | 82 | | | | | | 40,000.00 |
| 69 | አስቻለው አደፍርስ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | | | 40 | | | 400 | | 5,000.00 | 37,000.00 |
| 70 | ጉርምስ አላዩ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | 1 | | | 2 | | | | | 5,000.00 |
| 71 | ባዩ መኩሪያ | ›› | ›› | ›› | ›› | | | 1 | | | | | | | | 20,000.00 |



ፎቶ ግራፍ 2፡ መኖሪያ ቤታቸው የተቃጠለባቸው አርሶ አደሮች በተቃጠለው በታቸው ላይ ቆመው ይታያሉ፡፡ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ናኖ ወረዳ ናኖ አሎ ቀበሌ ውስጥ የተነሳ፣ 2007 ዓ.ም

**መ/ር ገረመው ናደው** ከላይ በተጠቀሰው ክልልና ዞን ውስጥ የእርሻ ስራ በመስራት በርካታ ንብረትና ቤተሰብ አፍርተው በአካባቢው ከ30 አመት በላይ ኖረዋል፡፡ በ2001 ዓ.ም በሀይል በከፍተኛ በደልና አስተዳደራዊ ጫና ቤት ንብረታቸውንና ቤተሰባቸውን ጥለው እንዲሰደዱ መደረጋቸው ህገወጥ ድርጊት እንደሆነና በአስቸኳይ መታረም እንደሚገባው ሰመጉ ከዚህ ቀደም ባወጣው መግለጫ መጠየቁ የሚታወቅ ነው፡፡[4] ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ምንም መፍትሄና ድጋፍ ሳያገኙ በመቅረታቸው በጎዳና ላይ በመንከራተት ላይ እንደሚገኙ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡



ፎቶ ግራፍ 3፡ መኖሪያ ቤታቸው ከተቃጠለባቸው አርሶ አደሮች ጥቂቶቹ በምስሉ ላይ ቆመው ይታያሉ፡፡ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ናኖ ወረዳ ናኖ አሎ ቀበሌ ውስጥ የተነሳ 2007 ዓ.ም

[4] የሰመጉ 128ኛ መደበኛ መግለጫ 2004 ዓ.ም አዲስ አበባ



ፎቶ ግራፍ 4፡ በእሳት የተቃጠለ የአርሶ አደር መኖሪያ ቤት ናሙና፣ ቦታ ኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ናኖ ወረዳ ናኖ አሎ ቀበሊ ውስጥ የተነሳ ፎቶግራፍ 2007 ዓ.ም

## 5. የመብት ጥሰቱ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ

የደረሰባቸውን የመብት ጥሰትና የተለያዩ አቢቱታቸውን መፍትሄ ይሰጡናል ለሚሏዋቸው ለተለያዩ የክልልና የፌዴራል ተቋማት በማቅረባቸው ለምን ከሰሳችሁን በማለት የተለያዩ አስተዳደራዊ ጫና፣ ዛቻ፣ ህገወጥ እስራት ጭምር እየተፈፀመባቸው እንደሚገኝና ለችግራቸው መፍትሄ የሚሰጣቸው የመንግስት አካል ባለመኖሩ ለከፋ ችግር እና እንግልት ተጋልጠው እንደሚገኙ ይህ ሪፖርት በመጠናቀር ላይ እያለ ለሰመጉ ገልፀዋል፡፡[5] ይህን መግለጫ ለማውጣት በመጨረሻው ሂደት ላይ እያለን፣ በዲኮሽሞ ቀበሌ የአቶ ደምስ መኩሪያና የአቶ በፈቃዱ ቢሰጠኝ መኖሪያ ቤቶች በእሳት እንዲቃጠሉ መደረጉን እንዲሁም ከአቤቱታ አቅራቢዎች መካከል ስምንት ሰዎች “ሽፍቶች ናቸው፣ ይታደኑ” የሚል ትዕዛዝ እንደወጣባቸውና በዚህም ምክንያት በፍርሐትና ሥጋት አካባቢያቸውን ለቅቀው እንደተሰደዱ ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

ዜጎችን “የአካባቢው ተወላጆች አይደላችሁም“ በማለት ያፈረሷቸውና ያቃጠሏቸው ቤቶች ነዋሪዎች ዚጎችና በሀገሪቱ አካባቢ ሁሉ ተዘዋውረው ኑሮ የመመስረትና ሐብት የማፍራት መብት እንዳላቸው በህገመንግስቱ ተደንግጎ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ

በአካባቢው የቀበሌና የፖሊስ ባለሥልጣናትና አባሎች መሪነት ቤቶቻቸው የተቃጠሉባቸው ነዋሪዎች፣ እንደማንኛውም ዜጋ በሀገሪቱ አካባቢ ሁሉ ተዘዋውረው ኑሮ የመመስረትና ሐብት የማፍራት መብት እንዳላቸው በህገመንግስቱ ተደንጓል፡፡ ነገር ግን ‹‹የዚህ ክልል ተወላጆች አይደላችሁም፣ ህገ-ወጦች ናችሁ›› ተብለው መኖሪያ ቤታቸው በህገወጥ መንገድ በእሳት እንዲወድም መደረጉ ከሃገሪቱ ህጎችና ከተቀበለቻቸው የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ጋር በእጅጉ ይቃረናሉ ብሎ ሰመጉ ያምናል፡፡ ይህ ችግር በዳርጌ ወረዳ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ውሰጥ በወረዳ፣ በቀበሌ ባለሥልጣናትና በሕግ አስፈጻሚና አስከባሪ አካላት የሚፈጸም መሆኑን ሰመጉ በተለያየ ጊዜ ካወጣቸው መግለጫዎች መመልከት ይቻላል፡፡

የዚህ የመብት ጥሰት ሰለባ የሆኑ ዜጎች ለረዥም አመታት ሰርተው ጥሪታቸውን በማፍሰስ የገነቧቸው መኖሪያ ቤቶች በማናለብኝነት በእሳት እንዲቃጠሉ በመደረጉ አሁንም ያለምንም የመንግስት እርዳታ በሜዳ ላይ ተበትነው

[5] የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው ተጎጅዎችና ተወካዮቻቸው ለሰመጉ ያቀረቡት አቤቱታ ቀን ሀምሌ 12 2007 ዓ.ም ቦታ አዲስ አበባ

ይገኛሉ። አቅመ ደካሞችና ህፃናት እየታመሙ፣ ያለ በቂ ምግብና መጠለያ ጎዳና ላይ መውደቃቸው ሰብአዊነትንና የህግ መርሆችን የሚፃረር በመሆኑ፣ መንግስት ለነዚህ ዜጎች በቂ ትኩረት በመስጠት ችግራቸው መፍትሄ የሚያገኝበትን መንገድ ከህዝቡ ጋር በመመካከር በአስቸኳይ እንዲፈልግ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

## 7. ማሳሰቢያ

መንግስት የዜጎቹ የኑሮ ሁኔታ በየጊዜው እየተሻሻለ በሚሄድ መልኩ ምግብ፣ መጠለያና ህክምና የማግኘት መብታቸውን የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ሰመጉ ያምናል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተተው አካባቢ ዜጎችም የዚህ መሰረታዊ መብት ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል። በማጠቃለያም መንግስት ከዚህ በታች የተገለፁትን እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲወስድ ሰመጉ ይጠይቃል።

እነዚህ ዜጎች ስለተፈጸመባቸው የመብት ጥሰት የተለያዩ አቤቱታዎችን በማቅረባቸው ብቻ እየደረሰባቸው ያለው ህገወጥ ድርጊት በአስቸኳይ መቆምና ለችግራቸውም አፋጣኝ መፍትሄ መሰጠት አለበት። በተለይም፡

- መኖሪያ ቤታቸው ለተቃጠሉባቸውና በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ለሚገኙት ዜጎች አስቸኳይ ሰብዓዊ እርዳታ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፣
- መኖሪያ ቤታቸው ለተቃጠሉባቸው ዜጎች ችግራቸውን በመገንዘብና በምክክር መኖሪያ ቤትና ለወደሙባቸው ንብረቶች ካሣ የሚያገኙበትን ሁኔታ መንግስት በአስቸኳይ ሊያመቻች ይገባል፣
- በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የጎሳና የዘር ልዩነትና አድልዎ እየተደረገባቸው እየተጎዱና እየተፈናቀሉ ያሉ ዜጎች ቁጥር በየጊዜው አሳሳቢ በሆነ መልኩ እየጨመረ ይገኛል። መንግስት ለዚህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የተጠናና የማያዳግም የመፍትሄ እርምጃ ከሕዝብ ጋር በመመካከር እንዲወስድ ሰመጉ አበክሮ ይጠይቃል።

ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመፃፍ ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል።

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል፡- kumashih@gmail.com
  ፋክስ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-23698፣ ፋክስ፡- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1370፣ ኢ-ሜል፡ justabr@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-7775፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-3620፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለደቡብ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- **ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

- **ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት**:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባህርዳር፣ ኢትዮጵያ

- **ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  ጅጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- **ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- **ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

[illegible]